# ሕዝብ ተነሳ!

የዘጋኸውን
ከፈተው በሩን

መልሰው ሀብቱን
የዘረፍከውን

እወቅ ታሪኩን
ያንኳሰስኸውን

አንሳ ሕግህን
የጫንክብንን

በቃ አገዛዝህ
ሂድ ወደጫካህ

ቤትህ ጫካነው
ሕዝብ የማያውቀው

ልቀቅ አልጋውን
የቀማኸውን

ሕዝብም ተነሳ
ክንድህን አንሳ

የቀበሮ ለምድ ለብሷል ወያኔ
እንዳትሳሳት ጠንክር ወገኔ

ገፏል ሙብትህን
ሰብአዊነትህን
ሰርቶ ምኖርክን
በአገር መኩራትህን

አንተን ሲያታልህ
ሲያጭበረብርህ
መልሶ ገዛህ
በአንጡራ ሀብትህ

ደመወዝ ከፋይ
እኔ ነኝ አለህ
ሲሻው‌ም
ቀማህ
ሲሻው አደለህ
ይኸን ሁሉ ግፍ
ዝም ብለህ አየህ

ሕዝብ ተነሳ
ክንድህን አንሳ

አድም አምፅ በስራ
ለሙብትህ ቁም ሁልህ በጋራ

በቁርኬ እህል እየሰፈሩ
መች በልተው ጠግበው ልጆች አደሩ

ቋትህም ደርቋል
ለማኝ ሁነሃል

ተነስ ለራስህ ከዚህ የባሰ ምን ይቀርሃል
እንደከብቶቹ ለጉመውሃል

ከመላኩ ፀጋዬ መኮንን